# የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኀብረሕዝብ አንድነት ንቅናቄ (ኢዴኀአን)
## መሥራች ጉባዔ የአቋም መግለጫ፤

## I. አጠቃላይ፤

የኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ ኅብረት (ኢዴኅ) እና የኢትዮጵያ ሕዝብ ፌዴራል ዴሞክራሲያዊ አንድነት ፓርቲ (ኅብረሕዝብ-ኢትዮጵያ) ቀደም ሲል ይፋ ባደረጉት እቅድ መሠረት የውኅደት ምሥረታ ጉባያቸውን ከታኅሣስ ፬ ቀን እስከ ታኅሣስ ፮ ቀን ፪ ሺህ ዓ/ም (December 14-16, 2007) በአሜሪካ አገር ሜሪላንድ ውስጥ አካሂደው የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኅብረሕዝብ የአንድነት ንቅናቄን (ኢዴኅአን ) መሥርተዋል።

መሥራች ጉባዔው ቀደም ሲል በውኅደት አመቻች አካሉ አማካይነት በተዘጋጁትና በሁለቱም ድርጅቶች አባላትና አካላት ታይተው በዳበሩት ሰነዶች (በፖለቲካ ፕሮግ-ግራሙ፥ በመተዳደሪያ ደንቡ፥ በመዋቅሩና በሥነ-ምግባር መመሪያው) ላይ ሰፊ ውይይት በማድረግ፥ የአጭር፥ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ የሥራ እቅዶች በማውጣት፥ ልዩ ልዩ ድርጅታዊ አካላትን በማቋቋምና ጊዚያዊ ኃላፊዎችን መርጦ በመሰየም መጠናቀቁን ስናበስር በታላቅ ደስታ ነው፡፡

ይኸ መሥራች ጉባዔ የተካሄደው የሕወሓት/ኢሕአዴግ መንግሥት አምባ-ገነን አገዛዙን በሕዝባችን ላይ እንዳሰፈነና የዜጎች ሰብዓዊ መብቶች ጥሰት በቀጠለበት፥ ቅድመ-ምርጫ የነበሩና በሕዝቡ ትግል በማቆጥቆጥ ላይ የነበሩ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ምሥረታ አስፈላጊና ችካል በሆኑ እንደ ነፃው ኅትመትና ስርጭት (ፕረስ) የመሳሰሉ ተቋማት እንዲከስሙ በተደረገበት፥ አገራችንና ሕዝባችን ወደባሰና ወደማያባራ የቀውስ አዙሪትና ትርጉም-የለሽ ጦርነት እየተወሰዱና ዓለም-አቀፍ ይዘት ባለው እጅግ ውስብስብና የአንድነት እጦት አደጋ በሚያንዥብብበት፥ ሕዝባችን አይከፍሉ ስቃይና መከራ አይቶና ከፍተኛ መስዋዕትነት ከፍሎ ያስገኛቸው ድሎች በተቀለበሱበት፥ የተቃዋሚው ጎራ አንድ ላይ መቆም አለመቻል ብቻ ሳይሆን ቅጥ ባጣ የውስጥ ነውጥ ውስጥ የሚገኝበትና ሁነኛ አመራር በገደደበት፥ ከላይ ሲታይ ለአምባ-ገነኖች ውርጅብኝ የተንበረከከና ተስፋ የቆረጠ ቢመስልም ሕዝባችን፥ በተለይም ወጣቱ ክፍል፥ የበጎ ሥርዓት ምኞቱንና ህልሙን ብቻ ሳይሆን በውስጡ ትግሉን በቁርጠኝነት እንደቀጠለበት ባለበት ሁኔታ ነው፡፡

ጉባዔው የአገራችንን ሁለንተናዊ ሁኔታ በመመርመርና በስፋትና በጥልቀት ውይይት በማድረግ አጠቃላይ ግንዛቤዎችን ወስዷል፥ ውሳኔዎችን አሳልፏል፥ ጥሪዎችንም አቅርቧል፡፡

## II. ግንዛቤዎች፤

1. የኢትዮጵያ ሕዝብ መሠረታዊ ሰብዓዊና ፖለቲካዊ መብቶቹን ለማስከበር የሚያደርገውንና ከፍተኛ መስዋዕትነት የከፈለበትን መራር ትግል አሁንም በልዩ ልዩ መልክ እንደቀጠለበት መሆኑን ፤
2. የሕወሓት/ኢሕአዴግ አምባ-ገነን የአገዛዝ ሥርዓት በሚከተላቸው ፖሊሲዎችና በሚወስዳቸው አሉታዊ እርምጃዎች ምክንያት ለተረጋጋና ለአስተማማኝ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ አስፈላጊ የሆኑ የሕግ የበላይነት፥ ተጠያቂነት፥ ግልጽነት፥ የሰብዓዊ መብት መከበርና ለእነዚህ እሴቶች መኖር፥ መጎልበትና በአስተማማኝ መቀጠል አስፈላጊ የሆኑ ተቋማት እንዲከስሙ እየተደረገ መሆኑንና በዚህ ረገድ የሚደረገው ጉዞ በአስደንጋጭ መልክ የኋሊት መሆኑን ጉባዔው አጢኗል፡፡ ስለሆነም የመንግሥት ሥልጣን የያዘው ሕወሓት/ኢሕአዴግ አገራችን ኢትዮጵያና ሕዝቧ ያሉባቸውን ዋና ዋናና ውስብስብ ችግሮች

ለመፍታት ብሔራዊ መግባባትን ሊያስገኝ ወደሚችል በእርቅና ሰላም ላይ የተመሠረተ ሽግግር ማካሄድ እንዳይችሉ ዋነኛ እንቅፋት መሆኑን፤

3. ውድ አገራችን ኢትዮጵያ ዓለም-አቀፍ ይዞት ባለው አንድነቷን አጥብቆ በሚፈታተንና ሕዝባችንን ለከፍተኛ ትርምስ ለሚያጋልጥ ከባድ የውጥረት ሁኔታ ውስጥ የምትገኝ መሆኑን፤
4. ሕዝባችን ብሶቱን ብሶቱ አድርጎ ያይልኛል፥ በመራር ትግሌና በከፈልኩት መስዋዕትነት ያገኘኋቸውን ድሎች ያስከብርልኛል፥ ብሎ ተስፋ የጣለበት የተቃዋሚ ጎራ የትግል አንድነት አጥቶና ይበልጥም በሚያሳዝን ሁኔታ የሕዝብንና የአገርን ሰቆቃ ያላቋጠረ በሚምስል መልኩ እርስ በርስ በሚደረግ ቅጥ ያጣ ሽኩቻ የተጠመደ መሆኑን፤

መሥራች ጉባዔው በከፍተኛ ቁጭት ተገንዝቧል።

## III. ውሳኔዎች፤

1. ሁለቱ ድርጅቶች - የኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ ኅብረት (ኢዴኅ) እና የኢትዮጵያ ሕዝብ ፌዴራል ዴሞክራሲያዊ አንድነት ፓርቲ (ኅብረሕዝብ) - ከታኅሣስ ፳ ቀን ፪ ሺህ ዓ/ም ጀምሮ የየግል ኅልውናቸ አክትሞ አንድ ድርጅት በመሆን የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኅብረሕዝብ አንድነት ንቅናቄን (ኢዴኅአን) መሥርተዋል።
2. ኢዴኅአን የቆመለትን አገራዊና ሕዝባዊ ዓላማ እውን ለማድረግ በአገር ውስጥ ለሚያደርገው እንቅስቃሴ ልዩ ትኩረት እንዲሰጥና በውጭና በውስጥ ያሉ አካላቱን በአጭር ጊዜ ውስጥ በተሻለ በማስተሳሰር ትግሉን ሁኔታና አቅም በፈቀደ በመላ የአገሪቱ ክፍሎች እንዲያካሂድ ወስኗል።
3. የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኅብረሕዝብ አንድነት ንቅናቄ (ኢዴኅአን) ከሌሎች አገር-ወዳድና ዴሞክራሲያዊ ኃይሎችና ወገኖች ጋር በመሆን የኢትዮጵያን አገራዊ አንድነትና የሕዝቧን ሁለንተናዊ መብቶች የሚያስከብር፥ የሕግ የበላይነትን የሚያስጠብቅ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እውን እንዲሆን ሕዝባችን የሰክነ ሰላማዊ ሽግግር እንዲያደርግ ሁኔታው በሚጠይቀው መንገድ የበኩሉን አስተዋጽዖ ለማድረግና ጠንክሮ ለመታገል ወስኗል።
4. ተዋኅደው ኢዴኅአን ያቋቋሙት ሁለት ድርጅቶች ከምሥረታው ጀምሮ አባል ሆነው የቆዩበት የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) አባል ሆኖ እንዲቀጥልና የኅብረቱ አባል ድርጅቶች የተሻለ ተቀራርበውና የጋራ ትግላቸውን የበለጠ እንዲያጎለብቱ የበኩሉን ከፍተኛ ጥረትና አስተዋጽዖ እንዲያደርግ ወስኗል።
5. በዚህ ረገድ ቀደም ሲል የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት አባል ከሆኑ ድርጅቶች ጋር የተደረገውን የመዋኀድ ውይይት እንዲገፋበትና ከኅብረቱ ውጭ ካሉ አገር-ወዳድና ዴሞክራሲያዊ ድርጅቶች፥ ቡድኖችና ስብስቦች ጋርም ውይይት በማድረግ በሁለቱ ድርጅቶች የተጀመረውን አዎንታዊ የውኅደት አቅጣጫ እንዲከተሉና የተቃዋሚውን ክፍል የሥርዓት ለውጥ አገራዊ ትግል እንዲያጎለብቱ ከፍተኛ ጥረት እንዲደረግ ጉባዔው ወስኗል።
6. በልዩ ልዩ ምክንያቶች ውኅደት መፈጸም ከማይችሉ አገር-ወዳድና ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ጋር የሲቪክና የሙያ ማኅበራትን ባካተተ መልኩ አገርና ሕዝብን ባስቀደመና በመቻቻልና በመከባበር መርኅ ላይ የተመሠረተ ሰፊና ጠንካራ ሁሉን-አቀፍ የተቃዋሚው ጎራ የትግል አንድነትና የጋራ መድረክ እንዲፈጠር ኢዴኅአን የበኩሉን ከፍተኛ ጥረት እንዲያደርግ ወስኗል።
7. አገራዊና ሕዝባዊ ትግሉ ተጠናክሮ ሕዝባችንን የድል ባለቤት ማድረግ የሚቻለው ተቃዋሚው ጎራ ሕዝብን ማዕከል ያደረገ ትግል ሲያደርግ ብቻ በመሆኑ፥ በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጭ የሚኖረው ታጋይ ሕዝብ ከምርጫ ፺፯ በፊትም ሆነ በኋላ የታየው የጋለ የለውጥ ስሜት፥ የወንድማማችነት/እህትማማችነት የአንድነት መንፈስ እንዲያንሰራራ ኢዴኅአን ድርሻውን በትጋት እንዲወጣና የሚችለውን ሁሉ እንዲያደርግ ጉባዔው ወስኗል።

**IV ጥሪ፤**

*ጉባዔው የሚከተሉትን ጥሪዎች ለኢትዮጵያ ሕዝብ፥ ለተቃዋሚው ክፍልና ለኢሕአዴግ መንግሥት ያቀርባል።*

*ሀ. ለኢትዮጵያ ሕዝብ፤*

*ታጋዩ፥ ታጋሹና አስተዋዩ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለፍትኅ፥ ለእኩልነት፥ ለሕግ የበላይነትና ለአንድነት ያደረከውና እያደረክ ያለኸው ትግል አርቆ ማየት በተሳናቸው ክፍሎችና በአምባ-ገነኖች እየተደናቀፈ የከፈልከውን መስዋዕትነት፥ ፍላጎትህንና ምኞትህን የሚመጥን ውጤት አላገኘህም። አሁንም የመንግሥት ሥልጣንን ብሔራዊ የኃላፊነት ስሜት-አልባ ከያዘው ክፍልም ይሁን በልዩ ልዩ ምክንያት ለልዩ ልዩ ግብ አገዛዙን በመቃወም ከሚታገሉት ተቃዋሚዎችና ተፋላሚዎች በኩል በሚሰነዘሩ እርምጃዎችና ዘመቻዎች ሳቢያ የወደፊት የጋራ ኀልውናህ፥ ቀጣይነት ያለው ሰላምህና እድገትህ ብቸኛና አስተማማኝ የሆነውን አንድነትህን ሳትሸረሽር፥ በወንድማማች/እህትማማች መንፈስ ለጋራ ዕድልህ በጋራ እንድትቆም ስናሳስብ፤ ቋንቋን፥ ጎሣን፥ አካባቢንም ሆነ ሐይማኖትን መሠረት ያደረገ ትግልም ሆነ በእነኝህ ልዩነቶች ላይ የተንጠለጠለ ክፍፍል የሚያረጋግጠው ነገር ካለ የጋራ ጥፋትና ውድቀትን ብቻ ነው። ለኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነቱ ጠላቱና ለድህነቱና ለብልጽግና ኋላ መቅረቱ ተጠያቂ ሆኖ አያውቅም፤ አይደለምም። የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለይ የነገይቱ ኢትዮጵያ ተረካቢ የሆነው ወጣቱ ወገናችን የአንድነት ትስስሩን እንዲጠብቅ ብቻ ሳይሆን እንዲያጠናክር ጥሪያችንን ስናቀርብ ከጠበቀ አደራ ጋር ነው። አንድነት ኃይል ነውና የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለመደው ጨዋነትህና አስተዋይነትህ ሳትከፋፈል የጋራ ዕድልህንና ኀልውናህን በጋራ ትግልህ እንድታስከብር ወገናዊ ጥሪያችንን በታላቅ አክብሮት እናቀርባለን።*

*ለ) ለተቃዋሚው ክፍል፤*

*ለአዎንታዊ ለውጥ የቆመው ወገን የሚያደርገው ትግል በጠራና ሕዝባዊነት ባለው መተክላዊ መርኀ-እቅድ (አጀንዳ) ላይ መመሥረትና እሱም መሆን ይኖርበታል ብለን እናምናለን። ትግሉ የሕዝብ መርኀ-እቅድን (አጀንዳን) ያነገበ ከሆነ ደግሞ ውስብስብ ፍልሚያን የሚጠይቀው የአገራችን ሁኔታ የሕዝባችንን እጣ ፈንታ የሚወስን መፍትኄን በተናጠልም ሆነ በተወሰኑ ድርጅቶች ጥረት ብቻ ማስገኘት ከቶውን አይቻልም። በአሁኑ ጊዜ በታጋይ ድርጅቶች መኻል የሚታየው መከፋፈል ሁሉም አትራፊና አቸናፊ ሊሆን የሚችልበትን ሥርዓት ሊያስገኝ ፈጽሞ አይችልም። ስሆነም የኢትዮጵያ ሕዝብ የዘመናት ሰቆቃ ተሰምቷቸው ለፍትኅ፥ ለእኩልነና ለአንድነት በልዩ ልዩ መልክ ለሚታገሉ ወገኖቻችን የምናሳስበው ቁም-ነገር ሁሉም አቸናፊና አትራፊ የሚሆንበት ሥርዓት ለማምጣት መቻቻልን፥ መከባበርንና 'እኔ ብቻ ተበዳይ፥ እኔ ብቻ ልክ ነኝ' የሚል አስተሳሰብን ማስወገድ የግድ እንደሚጠይቅ ነው። ማንኛውም ሁሉን ያላቀፈና አግላይ አካሄድ ብሔራዊ መግባባትን ሊፈጥር አይችልም። አንድ ወይም የተወሰነ ክፍል ብቻ አቸናፊ ከሆነ ሕዝባኘንን የተጠናወተው አሳዳጅ/ተሳዳጅ፥ አሳሪ/ታሳሪ፥ ወዘተ አዙሪት እንዲቀጥል ከማድረግ ውጭ የተለየ ውጤት የለውም። የመንግሥት ሥልጣን የያዘን ክፍል አስገድዶ ትርጉም ወዳለው ድርድር ለማምጣትና ኅብረተሰባችን የሰከነ ሰላማዊ ሽግግር እንዲያደርግ ከተፈለገ ሕዝብን ማዕከል ያደረገ ትግልን በአንድነት ማድረግ ያስፈልጋል። በመሆኑም ኢዴኅአን በአገራችን ዘለቄታዊነት ያለውና አስተማማኝ ሰላማዊ ለውጥ ለማምጣት የሚፈልግ አገር-ወዳድና ዴሞክራት ኃይል ሁሉ ቅጥ ያጣና ትርጉም የሌለው ክፍፍልን በማስወገድ፥ ትግሉ በመላው የኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ውስጥ ያሉ የፖለቲካ ኃይሎች፥ የሲቪክና የሙያ ስብሰቦችና የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች (ተማሪዎች፥ ወጣቶች፥ ወላጆች፥ ሴቶች፥ ነጋዴዎች፥ ገበሬዎች፥ ሠራተኞች፥ አገራዊና ወገናዊ ስሜት ያላቸው*

የሠራዊትና የፖሊስ ኃይል አባላት፥ ወዘተ... በሙሉ የሚተባበሩበት ሁሉን-አቀፍ የሆነ ሕዝባዊ እርብርብን የሚጠይቅ በመሆኑ፥ ከግለሰብ ቀርቶ ከቡድን በላይ ለሆነ የአገርና የወገን (የሕዝብ) ክቡር ዓላማ ቅድሚያ በመስጠት፥ በመከባበርና በመቻቻል መንፈስ የተቃዋሚው ጎራ ሃቀኛ የጋራ ትግል መድረክ በአስቸኳይ እንዲፈጠር ለሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶችና ለሲቪክና የሙያ ማኅበራትና ስብስቦች ወገናዊ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

ሐ) ለሕወሓት/ኢሕአዴግ መንግሥት፤

ሕወሓት/ኢሕአዴግ የአገሪቱን ማዕከላዊ የመንግሥት ሥልጣን ከያዘበት የታሪክ አጋጣሚ ጀምሮ የኢትዮጵያ ሕዝብ በእርቅና ሰላም ላይ የተመሠረተ ሰላማዊ ሽግግር በማድረግ ለዝንትዓለም ከተቆራኙት መሃይምነት፥ አንገት አስደፊ ችጋርና ኋላ-ቀርነት መላቀቅ የሚችልበትን አስተማማኝ ፈር ማስያዝ ሲችል እንዲያውም ከአንድነት ይልቅ ልዩነትን፥ የወጣው ጓጉቶ ወደ አገሩ እንዲመለስ ሁኔታዎችን ከማመቻቸት ይልቅ ዜጎች ታይቶ በማይታወቅ ደረጃ ከሲያል እንደምትሸሽ ነፍስ ከውድ አገራቸው ወደ ባዕድ አገሮች እንዲፈልሱ ማድረግን፥ ከብሔራዊ ጥቅምና ሉዓላዊነት ማስከበር ይልቅ አንድነቷ የተሸረሸረና የባሕር በር-አልባ እስረኛ አገር ማድረግን፥ ለአካባቢ ሰላምና መረጋጋት፥ መልካም ጉርብትናና ወዳጅነት ከማትረፍ ይልቅ ለአገር ጠላቶች ማብዛትን፥ ለሕዝብና ለታሪክ ከበሬታና ፍቅር ከማሳየት ይልቅ የሕዝብ ፍላጎትን መሻርና ተስፋውን ማጨለምን፥ በሕዝብ መኻል መተማመንና መተሳሰብን ከመፍጠር ይልቅ አለመተማመንና መጠራጠርን፥ ወዘተ... በበላይነት ሲያራምድ መቆየቱን የኢትዮጵያ ሕዝብ በሐዘኔታ የተመለከተው ጉዳይ ነው።

ኢዴኅአን በልዩ ልዩ ኃይሎች አገራችንና ሕዝቧ መጠነ-ሠፊና ፈርጀ-ብዙ በደሎችና ችግሮች ደርሶባቸዋል ብሎ ያምናል። ሆኖም ለሕዝባችን ካለፉት በደሎቹና ከደረሱበት ችግሮች የወደፊቱ የጋራ ዕድሉ በእጅጉ እንደሚበልጡበት እንገነዘባለን። ያለፉትን በደሎችና ግፎች ሁሉ ማንሳት ካለብን እንዳይደገሙ ትምህርትና ማስገንዘቢያ እንዲሆኑን እንጂ የበቀል አዙሪትን የሚጋብዝና የወደፊት የጋራ ዕድላችንን በጋራ ከመምከርና ከመወሰን እንዲያግዱን ሊሆን ከቶ አይገባም ብለን እናምናለን። ስለሆነም ሕዝባችን ዘለቄታዊ ሰላምና መረጋጋትን አግኝቶ የብልጽግና ጎዳናን እንዲይዝ ከሁሉ በፊት ከፍራቻ፥ ከርስ በርስ መጠራጠር፥ ካለመተማመን፥ ወዘተ... ነፃ መሆን ይኖርበታል። ማንኛውም ሕዝብ በአምባ-ገነን ሥርዓት ሥር እስካለ ድረስ ደግሞ ከነዚህ አሉታዊ ገጽታዎች ሊላቀቅ አይችልም። የሕወሓት/ኢሕአዴግ ቁንጮዎች መረዳት ያለባቸው በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚገዙት በፍላጎቱና በምርጫው ሳይሆን በአመጽና በጥሬ ጉልበት መሆኑን ነው። እንኳን በሃያ-አንደኛው ክፍለ-ዘመን ምን ጊዜም ቢሆን ሕዝብን በኃይልና በጉልበት ለረጅም ጊዜ ለመግዛት መሞከር ደግሞ ትርፉ አሰቃቂ ውድቀትን ማስከተል ብቻ እንደሆነ መረዳት ያስፈልጋል። ስለሆነም ሕወሓት/ኢሕአዴግ የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍላጎት ማክበር የሚኖርበት በይበልጥ ለራሱ እንደሆነ ልብ ይሏል። በማንኛውም መንገድ በሥልጣን ላይ ለመቆየት ያኽል ብቻ ሲባል የሚወሰዱ አገርና ሕዝብን የሚጎዱ እርምጃዎች መቆም ይኖርባቸዋል። ለሕወሓት/ኢሕአዴግ ቁንጮዎች በጎ ስም፥ ሥልጣንም ሆነ ድርጅታዊ ኅልውና ብቸኛ ዋስትና በሕዝብ ፈቃድ መመራትና መገዛት ብቻ ነው። ማንም ያምጣቸው ማን የአገራችን ችግሮች የጋራችን ናቸውና የሁላችንም የሆኑ ችግሮቻችን የሁላችንም የጋራ መፍትኄ ይሻሉና አሁንም ኢዴኅአን የሕወሓት/ኢሕአዴግ መንግሥት ሥልጣን ከያዘ ጀምሮ ከተቃዋሚው ክፍል ለቀረበለት ያልተቋረጠ ኃላፊነት የተመላበት የአገራዊ እርቅና ሰላም ጥሪ በጎ ምላሽ እንዲሰጥ እነሆ ጥሪውን ያቀርባል።

ለአገራችን አንድነትና ለሕዝባችን መብቶች መከበር በጋራ እንቁም!
ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኅብረሕዝብ አንድነት ንቅናቄ
ዋሽንግተን ዲ.ሲ. አሜሪካ
ታኅሣስ ፯ ቀን ፪ ሺህ ዓ/ም